የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፳፻፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 16
ADDIS ABABA, 31th January, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፩/፳፻፲፮

የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅ …....................................ገጽ ፲፯ሺ፮፻፳፬

## Content

Proclamation No. 1361/2024

The Green Legacy and Degraded Landscape Restoration Special Fund Establishment and Administration Proclamation….......Page 17624

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፩/፳፻፲፮

## የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የተጎሳቆለ መሬት መልሶ እንዲያገግም በማድረግ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን በመጠበቅና በመንከባከብ ለሀገራችን ዘላቂነት ያለው ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና የሥነ-ምህዳር ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ለአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች ቋሚና ተቋማዊ ሥርዓት ያለው የፋይናንስ አቅም እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዘላቂነት የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም እና ከአየር ንብረት ብክለት የፀዳ ኢኮኖሚ ለመገንባት የተያዘውን ሀገራዊ ራዕይ እንዲሳካ አስተዋፅኦ ማድረግ በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION No. 1361/2024

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE GREEN LEGACY AND DEGRADED LANDSCAPE RESTORATION SPECIAL FUND AND TO DETERMINE ITS ADMINISTRATION

**WHEREAS**, restoring degraded landscapes, protecting and conserving natural and manmade forest resources is fundamental to ensure their economic, social, and ecological benefits to the nation in a sustainable way;

**WHEREAS**, it is found necessary to establish a sustainable financing mechanism for green legacy initiatives;

**WHEREAS**, it is necessary to support the national vision to build climate-resilient and carbon neutral economy;

እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተቀናጀ ቋሚና ዘላቂነት ያለው የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ በመመደብና በማሰባሰብ ሁሉም ክልሎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሰራር መቀየስ ተገቢና ለዚህም የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፩/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ በተደነገገው መሰረት ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፪/ **"የሚመለከተው የስራ ክፍል"** ማለት በገንዘብ ሚኒስቴር የተባበሩት መንግሥታት ተቋማት፣ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ፋሲሊቲ እና የአህጉራዊ ኢኮኖሚ ትብብር የሥራ ክፍል ነው፤

**WHEREAS**, to be able to attain these objectives, it is vital to establish a coordinated and sustainable financing from domestic sources and put in place mechanisms to allocate funds to all regions in equitable ways and for this to happen it is found necessary to establish Green Legacy and Degraded Landscape Restoration Special Fund;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (l) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**l. Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Green Legacy and Degraded Landscape Restoration Special Fund Establishment and Administration Proclamation No.1361/2024".

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ **"Region"** means a region designated by Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and for the purpose of this Proclamation, it also includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

2/ **"Responsible Department"** means the United Nations Agencies, Climate Resilient Green Economy Facility and Regional Economic Cooperation Department within the Ministry of Finance;

፫/ **“አረንጓዴ አሻራ”** ከ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቋሚ ዕጽዋትን በሕብረተሰብ ተሳትፎ የማልማት ፕሮግራም ነው፤

፬/ **“የተጎሳቆለ መሬት”** ማለት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቱ የቀነሰና ምርታማነቱን ያጣ በመሆኑ የማገገም ስራዎች ሊሰሩበት የሚገባ መሬት ነው፤

፭/ **“የተጎሳቆለ መሬት ማገገም”** ማለት የተጎሳቆለ መሬትን ለደን ልማት እና ለጥምር ደን ግብርና እንዲውል ማድረግ ነው፤

፮/ **“ቀመር”** ማለት በፌደራል መንግሥት ለክልሎች ከተመደበው የልዩ ፈንዱ በጀት ላይ የያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግል ስሌት ነው፤

፯/ **“ተጓዳኝ በጀት”** ማለት ክልሎች የልዩ ፈንዱን ዓላማ ለማሳካት ከክልላቸው ገቢ በየዓመቱ በልዩ ፈንዱ ለሚደገፉ ፕሮጀክቶች የሚመድቡት በጀት ነው፤

፰/ **“ተጠቃሚ አካላት”** ማለት በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን የሚተገብሩ የፌደራል መንግሥት ተቋማት እና ክልሎች ሲሆኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንኡስ አንቀጽ (፪) መሠረት አብይ ኮሚቴው ለዚህ አላማ የሚያወጣውን መመዘኛ የሚያሟሉ ሌሎች አካላትን ይጨምራል፤

፱/ **“የልማት አጋሮች”** ማለት ለልዩ ፈንዱ የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የዓይነት ድጋፍ የሚሰጡ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ መንግሥታት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶችና ፋውንዴሽኖች ናቸው፡፡

3/ **“Green Legacy”** means a program that has been implemented since 2019 aiming at planting ecologically friendly multipurpose perennial species through citizen mobilization;

4/ **“Degraded Landscape”** means land that its ecological services diminished and has lost its productivity, and significantly and requires restoration;

5/ **“Restoration of Degraded Landscape”** refers to the restoration of degraded landscape for afforestation and agroforestry purposes;

6/ **“Formula”** means the calculation used to determine the share of each region from the budget allocated to the regions from the special fund;

7/ **“Matching budget”** means a budget that regions allocate every year from their regional revenue to projects, which are supported by the special fund to achieve the purpose of the special fund;

8/ **“Accessing Entities”** means Federal government institutions and regions, that implement projects supported by the special fund, and includes other entities that meet the criteria set by the steering committee for this purpose in accordance with Article 8 Sub-Article (2) of this Proclamation;

9/ **“Development Partners"** means international institutions, governments, non-governmental organizations, and foundations that provide financial, technical, and in-kind support to the Special Fund.

## ክፍል ሁለት

## ስለልዩ ፈንዱ መቋቋም

### ፫. መቋቋም

፩/ የአረንጓዴ አሻራ እና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ልዩ ፈንዱ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ልዩ ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለዚህ አዋጅ አላማ ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

### ፬. የልዩ ፈንዱ አላማዎች

ልዩ ፈንዱ የሚከተሉት ውስን ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የተጎሳቆለ መሬት በተፈጥሮና በመልሶ ማልማት መርህ በመታገዝ እንዲያገግም በማድረግ የደን ልማት እና የደን መልሶ ማልማትን መደገፍ፤

፪/ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እና በዜጎች ተሳትፎ የተተከሉ ችግኞች እና ያገገሙ መሬቶች ውጤታማ እንዲሆኑና ዘለቄታ እንዲኖራቸው መደገፍ፤

፫/ የደን ልማትና የደን ጥበቃ እንዲሁም ተዛማጅ የሥርዓት-ምህዳር አገልግሎቶችን በማሻሻል ለዜጎች በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች ዘላቂነት ያለው የሥራና የመተዳደሪያ ስራ ዕድል መፍጠር፤

፬/ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቋሚ ዕጽዋትን መሰረት በማድረግ የወንዞች፣ የግድቦችና ሌሎች የውሃ አካላት ዳርቻዎችን መልሶ ማልማት፤

፭/ የከተማ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት ሥራዎችን መደገፍ፤

## PART TWO

## Establishment of the Special Fund

### 3. Establishment

1/ The Green Legacy and Degraded Landscape Restoration Special Fund (herein after referred to as "the Special Fund") is hereby established by this Proclamation.

2/ The Special Fund shall serve as a permanent source of finance to achieve the objectives of this Proclamation.

### 4. Objectives of the Special Fund

The Special Fund shall have the following specific objectives:

1/ Support the restoration of degraded landscape through assisted natural regeneration and afforestation and reforestation to develop and restore forests;

2/ Enhance the sustainability and productivity of planted seedlings and restored landscapes through citizens mobilization and the Green Legacy initiative;

3/ Create employment opportunities and sustainable livelihoods in particular for the youth and women through forestry development, protection of forests improvment of ecological services;

4/ Develop riverbanks, areas around dams and other water bodies through locally adaptable perennial plants;

5/ Support urban beautification and greenery;

፮/ ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ የደን ዘርፍን ማዕከል ባደረገ መልኩ ለማሳካት ያቀደቻቸውን ግቦች፣ በተለይም የካርቦን ልቀት ቅነሳ ግብ እንዲሳካ አስተዋጽኦ ማድረግ፤

፯/ ከልማት አጋሮች ለደን ልማትና ጥበቃ የሚገኝ ድጋፍ እንዲጨምር ማድረግ፤

፰/ በልዩ ፈንዱ ከለማ ደን በዓለም አቀፍ የካርቦን ግብይት ሀገራችን ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፤

፱/ ከአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ እና ሥርዓት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምርምሮችና ፈጠራዎች መደገፍና አቅም መገንባት፡፡

**፭. <u>የልዩ ፈንዱ የፋይናንስ ምንጮች</u>**

ልዩ ፈንዱ ከሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

፩/ የፌደራል መንግሥት ከሚመድበው በጀት፤

፪/ ከልማት አጋሮች፣ ከሲቪክ ማህበረሰብ እና ከግል ዘርፍ ከሚገኝ ድጋፍ፡፡

**፮. <u>የፈንዱ ተሰብሳቢ ገንዘብ መጠንና ገንዘቡን ገቢ ስለማድረግ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለልዩ ፈንዱ የሚመደበው ገንዘብ የፌደራል መንግሥት በየዓመቱ ከሀገር ውስጥ ገቢ ምንጭ ከሚመድበው ዓመታዊ በጀት ውስጥ ከዜሮ ነጥብ አምስት እስከ ፩ በመቶ ያህል ይሆናል፡፡ የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ የሚመድበው ዓመታዊ በጀት የፌደራል መንግሥት ዓመታዊ በጀት አካል ሆኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይጸድቃል፡፡

6/ Contribute to the realization of Ethiopia’s international forest sector- goals, especially the objective of lowering carbon emissions;

7/ Mobilize additional resources from development partners for forest development and conservation;

8/ Enable Ethiopia to benefit from an international carbon financing mechanism from forests developed by the special fund;

9/ Support climate change adaptation and mitigation related capacity building, research and innovations.

**5. <u>Finance Sources of the Special Fund</u>**

The Fund shall be collected from the following financing sources:

1/ Budgetary allocations by the Federal Government;

2/ Support from development partners, civil society and the private sector.

**6. <u>Proportion and Depositing of the Special Fund</u>**

1/ The budget to be allocated to the special fund by the Federal Government as per Article 5 Sub-Article (1) of this Proclamation shall be between 0.5 to 1.0 percent of the annual budget allocated by the Federal Government from domestic revenue sources. The actual annual allocation to the special fund shall be approved by the House of People's Representatives as part of the annual Federal Government budget.

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለልዩ ፈንዱ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ በየሦስት ወሩ በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀማጭ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከልማት አጋሮች፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከግሉ ዘርፍ ለልዩ ፈንዱ የሚደረገው ድጋፍ የሚተዳደርበት አኳኋን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

## ፯. <u>የልዩ ፈንዱ የሀብት ክፍፍልና አለቃቀቅ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ የሚመድበው ዓመታዊ በጀት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ለፌደራል መንግሥት እና ለክልሎች ይደለደላል፡፡

፪/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለክልሎች ከሚደለደለው በጀት ላይ የእያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግለውን ቀመር አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ ሆኖም ለመሸጋገሪያ የፌደሬሽን ምክር ቤት ያጸደቀው ጠቅላላ የበጀት ድጋፍ ቀመር ከሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

2/ The budget allocated to the special fund by the Federal Government as per Article 5 Sub-Article (1) hereof shall be deposited every Three months into the bank account opened to the special fund by the Ministry of Finance.

3/ Support mobilized from development partners, civil society and the private sector for the Special Fund as per Article 5 Sub-Article (2) shall be administered in accordance with the procedures and guidelines to be issued by the Ministry of Finance.

## 7. <u>Allocation and Release of Funds</u>

1/ The annual budget allocated by the Federal Government to the special fund pursuant to Article 5 Sub-Article (1) hereof shall be appropriated to the Federal Government and the Regions in accordance with the criteria set by the Ministry of Finance.

2/ The Ministry of Finance shall prepare and submit to the House of Federation for approval, the formula to be used to determine the share of each Region from the portion of the budget of the Special Fund appropriated to the Regions in accordance with Sub-Article (1) hereof. However, for the transition, the general budget subsidy formula that the House of Federation issued may be applied for a period not exceeding Three years.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት ላይ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግለው ቀመር በገንዘብ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ከሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ጋር በሚደረግ ምክክር በሚደረስበት መግባባት መሰረት ይወሰናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከተደለደለው ዓመታዊ የሀብት ድርሻ ላይ በየሦስት ወሩ ወደ ተጠቃሚ አካላት ገንዘብ ሊተላለፍ የሚችለው፡-

ሀ) የሥራ አፈጻጸምን መሠረት በማድረግ፤

ለ) ክልሎች ተጓዳኝ በጀት ሲመድቡና በክልሉ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ፈሰስ ሲያደርጉ ይሆናል፤

ሐ) ክልሎች ከዚህ በላይ በፊደል ተራ (ለ) መሰረት የሚመድቡት ዝቅተኛ ተጓዳኝ በጀት ተፈጻሚ የሚሆነው በተጓዳኝ በጀቱ መጠን ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ በተዘረዘሩት አካላት መካከል በሚደረግ ምክክር የጋራ ስምምነት ሲደረስና በየክልሉና በከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤቶች ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተደነገገው መሰረት እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ሳይተላለፍ የቀረ ገንዘብ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ለልዩ ፈንዱ ከሚመደበው በጀት ጋር ተደምሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይደለደላል፡፡

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the share of the Addis Ababa and Dire Dawa City Administration from the budget allocated to the special fund by the Federal Government shall be prepared by the Ministry of Finance, with the final decision thereon being made in accordance with the understanding reached through consultation with the respective city administration.

4/ Without prejudice to Sub-Article (1) and (2) of this Article, quarterly disbursement of the allocated annual budget from the Special Fund to accessing entities shall be based on:

a) performance;

b) the regions allocating a matching budget and disbursing same to projects implemented in their respective Region/City Administration; and

c/ the allocation of the minimum matching budget by the Regions pursuant to Paragraph (b) above shall go into effect when consensus is reached on the proportion of the matching budget through consultation among entities specified in Article 10 hereof and upon approval thereof by the Council of Representatives of each region.

5/ Budget that has not been transferred until the end of the fiscal year as per Sub-Article (4) of this Article shall be combined with the budget allocated to the special fund of the following fiscal year and distributed in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

**፰. <u>የልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ አካላት</u>**

፩/ በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን የሚያስፈጽሙ የፌደራል መንግሥት አካላት እና ክልሎች ከልዩ ፈንዱ በቀጥታ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው በተጨማሪ አብይ ኮሚቴው በሚያወጣቸው መመዘኛዎች መሠረት ሌሎች አካላት ከልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**፱. <u>ስለ ልዩ ፈንዱ ሂሳብ</u>**

፩/ ተጠቃሚ አካላት በልዩ ፈንዱ ድጋፍ የሚተገብሯቸውን ፕሮጀክቶች የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በተመለከተ ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት መያዝ አለባቸው፡፡

፪/ ተጠቃሚ አካላት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ ከፌደራል መንግሥት የተላለፈላቸውን የልዩ ፈንዱን ገንዘብ አጠቃቀም የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅተው ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባሉ፡፡

፫/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከተጠቃሚ አካላት የሚቀበለውን የሂሳብ ሪፖርት በማጠቃለል የልዩ ፈንዱን ሂሳብ ዘግቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወራት ውስጥ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር በሚወክለው ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

**8. <u>Accessing Entities of the Special Fund</u>**

1/ The Federal government institutions and the regions that implement projects supported by the special fund shall directly access from the special fund.

2/ In addition to those mentioned in Article 8 Sub-Article (1) above, the Steering committee may set criteria to allow other entities to have direct access to the Special Fund.

**9. <u>Account of the Special Fund</u>**

1/ Accessing Entities shall keep an accurate and complete book of account of projects implemented with financial support obtained from the Special Fund.

2/ Accessing entities shall prepare a financial statement showing the use of the money of the special fund transferred to them by the Federal Government, within One month of the end of the fiscal year and submit same to the Ministry of Finance.

3/ The Ministry of Finance shall consolidate the financial statements it receives from accessing entities as per Sub-Article (2) of this Article, close the account of the special fund and submit the consolidated financial statement of the fiscal year to the Federal Auditor General or the auditor designated by it for examination within Three months of the end of the fiscal year.

፬/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ምርመራ አከናውኖ የኦዲት ውጤቱን እንዳሳወቀው የኦዲት ሪፖርቱን ለአብይ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ስለ ልዩ ፈንዱ አስተዳደር**

**፲. የልዩ ፈንዱ አስፈጻሚ አካላት**

የፈንዱ አስፈጻሚ አካላት የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት እንዲሁም የክልሎች የገንዘብ ቢሮዎች ናቸው፡፡

**፲፩. አብይ ኮሚቴ**

፩/ ልዩ ፈንዱ አጠቃቀሙና አተገባበሩን በበላይነት የሚቆጣጠር አብይ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

፪/ የአብይ ኮሚቴው አባላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ የተዘረዘሩት የልዩ ፈንዱ አስፈጻሚ አካላት የበላይ ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

፫/ የገንዘብ ሚኒስትርና የግብርና ሚኒስትር እንደቅደም ተከተላቸው የአብይ ኮሚቴው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡

፬/ የሚመለከተው የሥራ ክፍል የፈንዱን አስተዳደራዊ ስራዎች ያከናውናል እንዲሁም የአብይ ኮሚቴው ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

4/ The Ministry of Finance, as per Sub-Article (3) of this Article, shall submit the result of the audit report to the Steering Committee once the federal auditor general or the auditor designated by it informs the results of the audit.

**PART THREE**

**Administration of the Special Fund**

**10. Executive Organs of the Special Fund**

Executive Organs of the special Fund are the Ministry of Finance, the Ministry of Agriculture, the Ministry of Planing and Development, the Ethiopian Forest Development and Finance Bureaus' of the Regions.

**11. The Steering Committee**

1/ The Special Fund shall have a steering committee overseeing its use and Implementation.

2/ Members of the steering committee shall be heads of executive organs of the special fund specified in Article 10 of this Proclamation.

3/ The Ministers of Finance and Agriculture shall, in order of their sequence be the chairperson and vice chairperson of the steering committee.

4/ The responsible Department shall carry out the administrative functions of the fund and serve as the secretary of the steering committee.

**፲፪. <u>የአብይ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር</u>**

፩/ አብይ ኮሚቴው የልዩ ፈንዱን አጠቃቀምና አተገባበር ይቆጣጠራል፤

፪/ የልዩ ፈንዱን የፕሮግራም ማዕቀፍ፣ እስትራቴጂና መመሪያዎች ያጸድቃል፤

፫/ በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ያጸድቃል፤

፬/ የልዩ ፈንዱን አጠቃላይ አፈጻጸም ይገመግማል፤

፭/ የልዩ ፈንዱን የኦዲት ሪፖርት ውጤት ያዳምጣል፤ በሪፖርቱ መሰረት ተገቢው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

፮/ መቋረጥና መሰረዝ በሚገባቸው ፕሮጀክቶች ላይ ይወስናል፤

፯/ መመዘኛዎችን በማውጣት ተጨማሪ አካላት ከልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

**፲፫. <u>የአብይ ኮሚቴው ስብሰባዎች</u>**

፩/ የአብይ ኮሚቴው ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሰብሳቢው ሲጠራ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ በማንኛውም የአብይ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የአብይ ኮሚቴው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙት አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

**12. <u>Powers and Duties of the Steering Committee</u>**

1/ Oversees the use and implementation of the Special Fund;

2/ Approves the program framework, strategy, and directives of the Special Fund;

3/ Approves projects to be supported by the Special Fund;

4/ Reviews the overall performance of the Special Fund;

5/ Reviews the results of the Audit Report of the Special Fund and ensures that recommendations of the Audit report are duly implemented;

6/ Decides on projects that shall be discontinued or canceled;

7/ Sets criteria to allow more entities to acecess from the special fund.

**13. <u>Meetings of the Steering Committee</u>**

1/ The Steering Committee shall have One regular meeting annually. However, extraordinary meetings of the Steering Committee may be held at any time when called by the Chairman.

2/ The quorum shall be constituted when more than half the members are present at any Meeting.

3/ Decisions shall be made by a majority vote of those present. In case of a tie, the chairman shall have a casting vote.

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አብይ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

4/ Without prejudice to the provision of this Article, the Steering committee may adopt its own rules of procedure.

**፲፬. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር**

የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

፩/ ልዩ ፈንዱን ያስተዳድራል፤

፪/ በፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ በየዓመቱ የሚመደበውን በጀት መጠን ያቀርባል፣ የፌደራል መንግሥት ዓመታዊ በጀት አካል ሆኖ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤

፫/ የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት ላይ የክልሎች ድርሻ ለያንዳንዱ ክልል የሚከፋፈልበትን ቀመር አዘጋጅቶ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፤

፬/ የፌደራል መንግሥት ተጠቃሚ አካላትና ክልሎች የፌደራል መንግሥት ለልዩ ፈንዱ ከሚመድበው በጀት ላይ የሚያገኙትን ጥቅል ድርሻ የሚወሰንበትን መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱ መሰረት የበጀት ክፍፍሉን ያዘጋጃል፤

፭/ በፌደሬሽን ምክር ቤት ቀመር መሰረት የሚወሰነውን የእያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለየክልሉ ያሳውቃል፤

፮/ ልዩ ፈንዱ ለአምስት ዓመት የሚመራበት ሀገራዊ የፕሮግራም ማዕቀፍ በየአምስት ዓመቱ ተዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴው እንዲቀርብ ያደርጋል፤

**14. Powers and Duties of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance shall have the following powers and duties to:

1/ Administer the Special Fund;

2/ Recommend the amount of the budget allocated to the special fund each year and ensure its approval as part of the annual federal government budget;

3/ Prepare the formula on the basis of which the budget allocated by the Federal Government to the special fund is distributed to each region, submit the formula to the House of Federation for approval and implement same upon approval;

4/ Sets the criteria for determining the share of the Federal Government and the Regions from the Special Fund and prepares the budget accordingly;

5/ Informs each Region of its share determined according to the formula of the House of Federation;

6/ Ensures preparation of the National Program framework of the Special Fund every Five years and submitted to the Steering committee;

፯/ የልዩ ፈንዱን አስተዳደር፣ ፕሮግራም/ፕሮጀክት አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥርን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ከነዚህም ጋር በተያያዘ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያካሂዳል፤

፰/ በተጠቃሚ አካላት የተዘጋጁ የፕሮጀክት ጽንሰ ሀሳቦችና የፕሮጀክት ሰነዶች በሚመለከተው አካል ተገምግመው ሲቀርቡ በአብይ ኮሚቴው እንዲጸድቁ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ የግምገማ ውጤቱን ያሳውቃል፤

፱/ ተጠቃሚ አካላት ለጸደቁ ፕሮጀክቶች ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፣ በጀት ይለቃል፤

፲/ በልዩ ፈንዱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አጠቃላይ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

፲፩/ ከልማት አጋሮች፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከግል ዘርፍ ለልዩ ፈንዱ ድጋፍ ያሰባስባል፤

፲፪/ ከዓለም አቀፍ የካርቦን ንግድ ተጠቃሚ መሆን እንዲቻል በልዩ ፈንዱ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን መሰረት በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ስምምነት ይፈጽማል፤

፲፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ልዩ ፈንዱን ኦዲት ያስደርጋል፤

፲፬/ የልዩ ፈንዱን አብይ ኮሚቴ በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

7/ Issues Directives concerning the special fund administration, program/project management and financial administration, develops operational systems and conducts capacity-building in connection therewith;

8/ Recommends to the steering committee the approval of Project concepts and project proposals prepared by accessing entities after reviewed by relevant institution and announces the evaluation results;

9/ Ensures accessing entities to submit their annual plan and cash flow needs for approved projects and effect budget transfer as per the approved annual work plan;

10/ Monitors and evaluates the performance of projects financed by the Special Fund and produces a consolidated report;

11/ Mobilizes additional resources for the Special Fund from development partners, civil societies, and the private sector;

12/ Facilitates the conditions and makes agreements with the relevant parties for projects supported by the special fund to benefit from international carbon trade;

13/ Ensure the Special Fund to be audited in accordance with Article 9 Sub-Article (3) hereof;

14/ Chair the special fund steering committee.

**፲፭. የግብርና ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር**

፩/ የልዩ ፈንዱን አብይ ኮሚቴ በምክትል ሰብሳቢነት ይመራል፤

፪/ የልዩ ፈንዱን የቴክኒክ እስታንዳርድና አሰራር መመሪያ ያወጣል፣ ትግበራውን ይከታተላል፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ይሰራል፤

፫/ ልዩ ፈንዱ ለአምስት ዓመት የሚመራበትን ሀገራዊ የፕሮግራም ማዕቀፍ በየአምስት ዓመቱ ከኢትዮጵያ ደን ልማት ጋር በመሆን የሚመለከታቸውን በማሳተፍ ያዘጋጃል፤

፬/ በዚህ አዋጅ ለኢትዮጵያ የደን ልማት የተሰጡ ተግባራትንና ሀላፊነቶችን ይከታተላል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**፲፮. የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር**

፩/ የልዩ ፈንዱን የፕሮግራም ማዕቀፍ ዕቅድ ይገመግማል፣ የግምገማውን ውጤት ያሳውቃል፤

፪/ የልዩ ፈንዱን የፕሮግራም ማዕቀፍ አፈጻጸም የመካከለኛና ማጠናቀቂያ ግምገማ ያከናውናል፡፡

**፲፯. የኢትዮጵያ የደን ልማት ስልጣንና ተግባር**

፩/ የልዩ ፈንዱ የፕሮጀክት ጽንሰ ሀሳብና የፕሮጀክት ሰነድ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ይገመግማል፣ የውሳኔ ሀሳብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

**15. Powers and Duties of the Ministry of Agriculture**

1/ Serves as a vice chairman of the Steering Committee;

2/ Issues directives on technical standards and implementation manuals for the Special Fund follow up its implementation and conduct capacity building in connection herewith;

3/ Prepares the Five-year national program framework that guides the special fund in conjunction with the Ethiopian Forestry Development and with the participation of the relevant stakeholders;

4/ Follows up, oversees and renders support to the Ethiopian Forestry Development in connection with the discharge of functions and responsibilities assigned to it in this Proclamation.

**16. Powers and Duties of the Ministry of Planning and Development**

1/ Appraise the Program framework plan of the Special Fund and notify the result;

2/ Undertakes mid-term and terminal evaluation on the implementation of the Program framework of the Special Fund.

**17. Powers and Duties of the Ethiopian Forestry Development**

1/ Causes the submission of concept notes and project documents, reviews together with relevant inistitutions and submit its recommendations to the Ministry of Finance;

፪/ በልዩ ፈንዱ ሊለሙ የሚችሉ ቦታዎች የሚለዩበትና የሚተከሉ የችግኝ ዝርያዎች የሚመረጡበትን አሰራር ያዘጋጃል፣ ክልሎችን ይደግፋል፤

፫/ በልዩ ፈንዱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ከዓለም አቀፍ የካርቦን ገበያ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ አስፈላጊውን የመነሻ እና የልኬት፣ የሪፖርት እና የማረጋገጥ ሥራዎች እንዲጠናቀቁ ያደርጋል፤

፬/ በልዩ ፈንዱ ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ያስገኙትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ፣ የካርቦን ልቀት ቅነሳ እና ሥርዓት-ምህዳራዊ ጠቀሜታ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

፭/ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራትና ሀላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፲፰. <u>ተጠቃሚ የፌደራል መንግሥት ተቋማት</u>

በልዩ ፈንዱ ተጠቃሚ የሆኑ የፌደራል መንግሥት ተቋማት የሚተገብሯቸውን ፕሮጀክቶች ፅንሰ ሀሳብና የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅተው ያቀርባሉ፣ ሲፀድቅም ይተገብራሉ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ፣ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

፲፱. <u>በልዩ ፈንዱ ለሚደገፉ ፕሮጀክቶች የክልሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ክልሎች፡-

፩/ ለልዩ ፈንዱ ተጓዳኝ በጀት በየዓመቱ ይመድባሉ፤

፪/ ለልዩ ፈንዱ የሚለሙ ቦታዎችን ይመርጣሉ፤ ያዘጋጃሉ፤ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጣሉ፤

2/ Prepares technical guidelines for site selection and identification of species to be planted by projects supported by the Special Fund, and provide support to the Regions;

3/ Gathers baseline data and put in place a Measurement, Reporting, and Verification (MRV) system for projects financed by the Special Fund to benefit from international carbon markets;

4/ Prepares report on the socio-economic and ecological significance as well as on carbon emission reduction contributions of projects financed by the Special Fund;

5/ Conducts capacity building activities to discharge the functions and responsibilities assigned to it in this Proclamation.

**18. <u>Accessing Entities of the Federal Government</u>**

Accessing entities of the Federal Government shall prepare and submit concept notes and project proposals, implement the same upon approval, monitor its progress and submit report.

**19. <u>Duties and Responsibilities of the Regions for Projects Supported by the Special Fund</u>**

The Regions shall:

1/ Allocate annually the matching budget for the Special Fund;

2/ Select sites for the implementation of projects financed by the Special Fund, prepare the same and issue land use certificate;

፫/ በልዩ ፈንዱ በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ማህበረሰቦችን በተለይም ሴቶችና ወጣቶችን ያደራጃሉ፣ ህጋዊ ዕውቅና ይሰጣሉ፤

፬/ በልዩ ፈንዱ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ፅንሰ ሀሳብና የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅተው ያቀርባሉ፣ ሲጸድቅም ይተገብራሉ፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላሉ፣ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

**፳. <u>የልዩ ፈንዱ አስተዳደር በጀት</u>**

ልዩ ፈንዱን ለማስተዳደር የሚያስፈልገው በጀት በየዓመቱ ከልዩ ፈንዱ የሚመደብ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፳፩. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፪. <u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የገንዘብ ሚኒስቴር ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ Organize members of the communities, in particular women and youth, who will be beneficiaries of projects supported by the Special Fund and give legal recognition thereto;

4/ Prepare and submit concept notes and project proposals to be implemented using financial support from the Special Fund, implement the projects upon approval, monitor their progress and submit reports on their implementation.

**20. <u>Budget for Administering the Special Fund</u>**

The Budget for administering the special fund shall be allocated annually from the special fund.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>Miscellaneous Provisions</u>

**21. <u>Inapplicable Laws</u>**

No law and customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

**22. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry of Finance may issue Directives for the implementation of this Proclamation and the Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**፳፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

**23. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its Publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 31th day of January, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**